

Ministry Of External Affairs
Government Of India
ECONOMIC DIPLOMACY & STATES DIVISION

# Aatmanirbhar Bharat

የሪፎርም ማበረታቻ

Ministry Of External Affairs
Government Of India

ECONOMIC DIPLOMACY & STATES DIVISION

# የህንድን አቅም ለማሳደግ 21 ትሪሊየን ሩፒ የማነቃቂያ ገንዘብ

ጠቅላይ ሚኒስቴር ሽሪ እና ሬንድራ ሞዲ በግንቦት 12 21 ትሪሊየን ሩቢ /277 ቢሊየን ዩኤስ ዶላር የሚያህለውን ገንዘብ ለማነቃቂያ ፓኬጅ ያስተዋወቀ ሲሆን ይህም የህንድ ጂዲፒ 10 በመቶ አካባቢ የሚሆን ገንዘብ ሲሆን ይህም የሚያገለግለው በኮሮና ቫይረስ /ኮቪድ 19/ ወረርሽኝ የተጐዱ ሰዎችን ለመርዳት እና አዲስ የንግድ የኢንቨስትመንት እና የስራ መንገዶችን በኢኮኖሚ ውስጥ ለመክተት ነው፡፡

እንደ ማነቃቂያ ፓኬጁ አካል ሰፊ የሪፎርም እና የድጋፍ እርምጃዎች ተግባራዊ ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን ይህም በህንድ ሀገር ውስጥ ከኮሮና ቫይረስ በሽታ በኋላ እኩል እድገት እና መሻሻል እንዲኖር ለማገዝ ነው፡፡ የተሻሻሉ ነፃነት፣ የፖሊሲ ማሻሻያዎች፣ የማቅለያ ደንቦች፣ የመሰረተ ልማት ኢንቨስትመንት፣ የክህሎት ልማት እና ወዘተ የወደፊቷን ህንድ የሚገነቡ ነገሮች ናቸው፡፡

ጠንካራ እና ማገገም የሚችል ህዝብ ሊኖር የሚችለው በመላው አለም ያሉ የሕንድ አጋሮች በንቃት ትብብር ሲያደርጉ ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ ማዕከላዊ መንግስቱ “የፀሐፊዎች አቅም ያለው ቡድን እና የፕሮጀክት ልማት ሴሎች” የሚሉትን በሚኒስትሮች እና መምሪያዎች ውስጥ ያዘጋጀ ሲሆን ይህም አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ወደ ህንድ ለመሳብ ነው፡፡



# የፀሀፊዎች አቅም ያለው ቡድን (EGoS)

- የፀሐፊዎች አቅም ያለው ቡድን እና የፕሮጀክት ልማት ሴሎች ከተለያዩ ሚኒስትሪዎች/መምሪያዎች የተውጣጡ በህንድ ውስጥ ኢንቨስትመንቶችን ለማሳደግ የቀረበው ምክረ ሀሳብ አካል ናቸው፡፡
- የፀሐፊዎች አቅም ያለው ቡድን እና የፕሮጀክት ልማት ሴሎች የጠቅላይ ሚኒስቴር ሞዲን የ5 ትሪሊየን ዶላር ኢኮኖሚ ራዕይን እውን ለማድረግ ጠቃሚ እርምጃ ናቸው፡፡
- ማበረታቻው ህንድ የበለጠ ባለሀብቶች የሚወዷት መዳረሻ እንድትሆን እና የወደፊት የተሳለቀ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲኖር የሚያደርግ ነው፡፡

- ይህም በሚኒስትሮች እና በማዕከላዊ የክልል መንግስታት በኢንቨስትመንት/ በማትጊያ ፖሊሲዎች የሚረዳቸውን የመደመር ሀይል ይሰጣል፡፡

- የውጭ ሀገር ተሳትፎ በሚጨምርበት ጊዜ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን እና ስራን ያሻሽላል፡፡

በዚህ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ውስጥ ህንድ ኢንቨስትመንቶቻቸውን ወደ አዳዲስ ቦታዎች ለማስፋፋት ለሚፈልጉ እና ስጋቶችን ለመቅረፍ ለሚፈልጉ ኩባንያዎች ኤዲአይን የመሳብ እድል አቅርባለች፡፡ የእነዚህን አይነት እድሎች ለማብቃት መንግስት ከኢንቨስትመንት ጋር የሚሄደውን ስነ ምህዳር ይህም የውጭ ሀገር ተሳታፊዎችን እንዲሁም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የሚደግፈውን ስርዓት ለመተግበር ወስነዋል፡፡

- መንግስት በህንድ ውስጥ የተለያዩ አይነት ምርቶች እንዲኖሩ እና በዩኤስ እና በኢዩ ወዘተ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ በገበያው ማገልገል እንዲችል ከፍተኛ እድገት አድርጓል፡፡
- እቅዱ ህንድን በአለም አቀፍ የዋጋ ትስስር ውስጥ ከፍተኛውን ሚና እንድትጫወት ለማድረግ ከአለም ኢኮኖሚ ውስጥ ያሉ እድሎችን ለማግኘት ያቀደ ነው፡፡



Ministry Of External Affairs
Government Of India

ECONOMIC DIPLOMACY & STATES DIVISION

# የፀሀፊዎች አቅም ያለው ቡድን (EGoS)

በህንድ ውስጥ ላሉት የውጭ ሀገር ባለሀብቶች ድጋፍ ለመስጠት እና በኢኮኖሚው ቁልፍ ሴክተሮች ውስጥ ያለውን እድገት ለመጨመር አቅም ያለው የፀሐፊ ቡድን የሚከተሉት የመሪነት ሚና አለው፡፡

- የካቢኔ ፀሐፊ (ሰብሳቢ)
- ዋና ስራ አስፈፃሚ NitiAayog (አባል)
- የፕሮሞሽን ኢንዱስትሪ እና የሀገር ውስጥ ንግድ መምሪያ ፀሐፊ (የአባል ሰብሳቢ)
- የንግድ መምሪያ ፀሐፊ (አባል)
- የገቢ ክፍል ፀሐፊ (አባል)
- የኢኮኖሚ ጉዳዮች ክፍል ፀሐፊ (አባል)
- የሚመለከተው ክፍል ፀሐፊ (ደጋፊ)

የባለሙያዎቹ ቡድን በህንድ ሀገር ውስጥ በሚገኙ እድሎች እና የኢኮኖሚ ጥንካሬዎች ዙሪያ ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች ምሪት የሚሰጡ ሲሆን ይህም ያለውን ጥሩ ልምድ ለማረጋገጥ እና የህንድ ተሳታፊዎች በድህረ ኮሮና ቫይረስ በአለም ገበያ ውስጥ ላለው ፍላጐት የሚመጥን አቅም እንዲኖራቸው መምራት

አቅም ያላቸው ፀሐፊዎች ቡድን አላማዎች:

- ከተለያዩ መምሪያዎች እና ሚኒስትሮች የመደመር ሀይልን ለማምጣት እና በየጊዜው የሚሰጠውን መግለጫ ማረጋገጥ
- በህንድ ሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት መስብ እንዲጨምር ለማድረግ እና በአለም ዙሪያ ላሉ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፋሲሊቲ ለማቅረብ
- ኢላማ ባደረገ መልኩ ለኢንቨስትመንቶች ማመቻቸት እና በአካባቢውም የፖሊሲ መረጋጋት መፍጠር
- በሚከተሉት መሰረት በየስራ ክፍሎቹ የተሰሩ ኢንቨስትመንቶችን መገምገም
  - የፕሮጀክት ፈጠራ
  - ትክክለኛ ኢንቨስትመንቶች
- መምሪያዎቹ የተለያዩ ደረጃዎችን እንዲያጠናቅቁ አቅም ባለው ቡድን ኢላማዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡

# የፕሮጀክት ልማት ሴሎች (PDC)

የፕሮጀክት ልማት ሴል ከማዕከላዊ መንግስት እና ከክልል መንግስት ጋር በመሆን ኢንቨስት ሊደረግባቸው የሚችሉትን ፕሮጀክቶች በማረጋገጥ በህንድ ሀገር ውስጥ ኢንቨስት ሊደረጉ የሚችሉትን ፕሮጀክቶች መስመር በመቀየስ የኤፍዲአይ ፍሰቱን ያሳድጋል።

የፕሮጀክት ልማት ሴሉ በጽንሰ ሀሳብ ያስቀምጣል፣ ስትራቴጂ ያወጣል፣ ይተገብራል እንዲሁም ዝርዝሮቹን ከተግባራዊ ፕሮጀክቶች አንፃር ያሰራጫል።

የፕሮጀክት ልማት ሴሎች
አላማ :

- ፕሮጀክቶችን ከነማረጋገጫቸው መፍጠር እና የመሬት መገኘት ከነቦታው እንዲሁም የተሟላ ዝርዝር የፕሮጀክት ሪፖርቶችን ለባለሀብቶች ስራ/ኢንቨስትመንት.
- ኢንቨስትመንቶችን ለመሳብ እና ለማስፈፀም መፈታት ያለባቸውን ጉዳዮች መለየት እና ያሉትን ችግሮች አቅም ባለው ቡድን ፊት ማምጣት

ሴሉ ህንድ በተሻለ ሁኔታ የባሀብቶች መዳረሻ እንድትሆን ማድረግ እና በጠቅላይ ሚኒስቴሩ እንደተቀመጠው ኢኮኖሚውን የማሳደግ ግንባታ ተልዕኮውን መደገፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ለህዝቦች የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ሲሆን ትልቅ እና የተለያየ ቀጥተኛ/ተዘዋዋሪ የስራ እድሎችን ይከፍታል።



# የህንድ የጥቃቅን አነስተኛ እና መካከለኛ  ኢንተርፕራይዞች ኢንዱስትሪውን ማሳደግ



የጥቃቅን፣ አሰነትኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ሕጉ በ2006 ከወጣ ከ14 አመት በኋላ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ  ኢንተርፕራይዙ እድሎችን እንዲያሳድግ ሆኖ ተሻሽሏል፡፡ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ሚኒስቴር ለዚህ ለጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አዲስ ምድብን ለመተግበር እየሰራ ሲሆን ይህም ለህንድ ስራ  ፈጣሪዎች አዲስ ገበያ ለመፍጠር የገንዘብ ማስገኛ መንገዶችን ይከፍትላቸዋል፡፡

- የማይክሮ ማኑፋክቸሪንግ እና አገልግሎቶች ትርጓሜ ወደ 10 ሚሊዮን ሩፒ ኢንቨስትመንቶች እና  ወደ 50 ሚሊየን ሩፒ ትርፍ አድጓል፡፡
- የአነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ እና አገልግሎቶች ገደብ ወደ 100 ሚሊዮን ሩፒ ኢንቨስትመንቶች እና  ወደ 500 ሚሊየን ሩፒ ትርፍ አድጓል፡፡
- የመካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ እና አገልግሎቶች ገደብ ወደ 200 ሚሊዮን ሩፒ ኢንቨስትመንቶች እና  ወደ 1 ቢሊየን ሩፒ ትርፍ አድጓል፡፡
- በሰኔ 1 ላይ በቀረቡ የኢንዱስትሪ ጥያቄዎች የመካከለኛ ድርጅቶች ትርጓሜ ወደ 500 ሚሊዮን ሩፒ እና  ወደ 2.5 ቢሊየን ሩፒ ትርፍ አድጓል፡፡ .

- የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ሪፎርም የማኑፋክቸሪንግ እና የአገልግሎቶች ኢንተርፕራይዞችን በመለየት አሁን ያለውን ፍላጐት ለማገልገል ሰርቷል፡፡
- ትርፍን ለማስላት አዲስ መስፈርት የወጣ ሲሆን ይህም  ወደ ውጭ የሚላኩትን ከትርፍ ውስጥ የማያካትት ሲሆን ይህም ደግሞ የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የበለጠ መላክ እንዲችሉ ነው፡፡
- ይህም የበለጠ የእድገት እና የኢኮኖሚ ስራውን እና የስራ ፈጠራዎችን እየመሩ ካሉ ሀገራት ወደሚመጡት ኤክስፖርቶች በደንብ እንዲጨምር ይጠበቃል፡፡

የጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች  ሚኒስቴር ለእነዚህ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ  ኢንተርፕራይዞች ጠንካራ የአያያዝ ዘዴን ያስቀመጠ ሲሆን እንዲሁም ሻምፒዮኖችን በሚለው ስም አዳዲስ ስራ ፈጣሪዎችን አስቀሙጧል፡፡ (www.champions.gov.in)

# በግብርና ምርት ከጉድለት የፀዳ ንግድ

የህንድ ህብረት ካቢኔ በሰኔ 3 የግብርና ምርት ንግድ እና የንግድ አሰራር (ማስታወቂያ/ማመቻቸት) ሕግ 2012ትን ያፀደቀ ሲሆን ይህም በግብርና ግብይት ውስጥ ያሉትን ገደቦች የሚያላላ ነው፡፡

**ጥቅሞች**

- ሕጉ አርሶ አደሮች እና ነጋዴዎች በግብርና ንግድ ውስጥ የምርጫ ነፃነትን ሊጠቀሙበት የሚችሉበትን ስነ ምህዳር ይፈጥራል፡፡
- ይህ ሕግ ለክልሎች እና በክልሎች መካከል እንዲሁም በክልሉ ውስጥ ንግድ እና የንግድ ስራዎችን ማከናወን እና በውጭ ግብይቶችን ማካሄድ ያስችላል (በክልል የግብርና ምርት ግብይት ሕጎች ውስጥ ተገልጿል፡፡)
- ይህ ሕግ ለአርሶ አደሮች ተጨማሪ ምርጫዎችን የሚከፍት ሲሆን የግብይት ወጪዎችን በመቀነስ የተሻሉ ዋጋዎችን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡
- አርሶ አደሮች ምርታቸው እንዲጨምር እና እጥረት ካለባቸው እና የዋጋ ቅናሽ ካለባቸው ክልሎች የተሻለ ዋጋ እና ደንበኞች እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል፡፡
- ሕጉ በግብይት መድረኮች ላይ የኤሌክትሮኒክ ንግድን የሚያስተዋውቅ ሲሆን ይህም አምሳያ የሌለውን የኤሌክትሮኒክ ንግድ ያረጋግጥላቸዋል፡፡
- አርሶ አደሮች በዚህ ህግ ስር በምርት ሽያጭ ላይ ክፍያ አይጠየቁም፡፡ የግጭት አፈታት ዘዴም አለ፡፡

## አንዲት ሕንድ፣ አንድ የግብርና ገበያ

ሕጉ ከኤፒኤምሲ ገበያ ውጭ ተጨማሪ የንግድ እድሎችን ለመፍጠር አላማ ያደረገ ሲሆን ይህም አርሶ አደሮች ለተጨማሪ ውድድር የተነሳ የጥሩ ክፍያ ዋጋዎችን ለማግኘት እንዲችሉ ነው፡፡

ይህም ያለውን የኤፒኤምሲ የግዢ ስርዓት ላይ ተጨማሪ በመሆን ለአርሶ አደሮች የተረጋጋ ገቢ ይሰጣል፡፡

# በአስፈላጊ ምርቶች ሕግ ላይ ማሻሻያ ማድረግ

Ministry Of External Affairs
Government Of India

ECONOMIC DIPLOMACY & STATES DIVISION

የሕንድ ህብረት ካቢኔ በሰኔ 3 ላይ የአስፈላጊ ምርቶች ሕግን ያሻሻለ ሲሆን ይህም በግብርና ለውጥ እና የአርሶ አደሮች ለውጥ ላይ ታሪክ እርምጃ ሲሆን እንዲሁም ከኮሮና ቫይረስ በኋላ የአርሶ አደሩን ገቢ የሚያሳድግ ነው። ይህ እርምጃ ምርቶችን ወደ ውጭ ለሚልኩ ላኪዎች እና በግብርና ንግድ/የመሰረተ ልማት ቦታ ላይ ለሚሰሩ ባለሀብቶች የተሻለ ኢኮኖሚ ያቀርባል።

**ጥቅሞች**

- የአስፈላጊ ምርቶች ሕግ ማሻሻያ ሲደረግ እንደ አገዳ እህል፣ ጥራጥሬ፣ የዘይት እህል፣ የምግብ ዘይቶች፣ ሽንኩርት እና ድንች የመሳሰሉት ከዚህ ከአስፈላጊ ምርቶች ዝርዝር ውስጥ ይወጣሉ። ይህም ደግሞ ለባለሀብቶቹ የተሻሻለውን ነፃነት ይሰጣቸዋል።
- የማምረት፣ ንብረት መያዝ፣ ማንቀሳቀስ፣ ማከፋፈል እና የማቅረብ ነፃነቱ የኢኮኖሚ ደረጃውን ወደማደግ የሚያመራ እና የግል/የውጭ ኢንቨስመንቱን ወደ ግብርናው ዘርፍ የሚስብ ይሆናል። እንዲሁም በቀዝቃዛ ማከማቻዎች/ የአቅርቦት ሰንሰሎቶቹ ያለውን ኢንቨስትመንት ለማሳደግ ይረዳል።

**የደንበኞችን ጥቅም ማስጠበቅ**

- በማሻሻያው ውስጥ እንደ ጦርነት፣ ረሃብ፣ ከፍተኛ የዋጋ ንረት፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ የግብርና ምርቶች ምግብ የመሳሰሉት ሁኔታዎች ላይ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።
- ይሁን እንጂ የተዘረጋው የዋጋ ሰንሰለት አቅም ከተሳታፊ ጋር የሚያገናኝ ሲሆን የላኪዎች የመላክ ፍላጎትም በዚህ አይነት የክምችት ገደብ ውስጥ የማይገሉ ሲሆን ይህም ደግሞ ባለሀብቶችን ለመጠበቅ ነው።
- ማሻሻያው የዋጋ መረጋጋትን በማምጣት እና የውድድር ገበያ አካባቢን በመፍጠር አርሶ አደሮችን እና ተጠቃሚዎችን የሚረዳ ይሆናል። እንዲሁም የግብርና ምርት ብክነትን ይከላከላል።

# ወደ ገበያ ለመግባት አቅም ያላቸው አርሶ አደሮች

Ministry Of External Affairs
Government Of India
ECONOMIC DIPLOMACY & STATES DIVISION

በዋጋ ማረጋገጫ እና የግብርና አገልግሎቶች ሕግ ላይ በ2012 የተደረገው የአርሶ አደሮች ስምምነት /የማብቃት እና መጠበቅ/ በግብርና ስራዎች ውስጥ ያሉትን ስጋቶች የሚያመጣጥን መሆኑ ተረጋግጧል።

## ጥቅሞች

- ሕጉ አርሶ አደሮች የማቀነባበሪያ ስራ ከሚሰሩት፣ ከጅምላ ሻጮች፣ ከጠቅላላ ንግዶች፣ ከትላልቅ ችርቻሮዎች፣ ከላኪዎች እና ወዘተ ጋር እንዲሰሩ አቅም ይሰጣቸዋል።
- ለአርሶ አደሩ የገበያን የማይገመት ችግር የቀረፈ ሲሆን ይህንንም ወደ ስፖንሰሩ አስተላልፏል። እንዲሁም አርሶ አደሩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የተሻለ ግብአቶችን እንዲያገኝ አስችሎታል።
- ሕጉ የግል ኢንቨስትመንቱን ለመሳብ የሚረዳ ሲሆን የህንዳዊያንን የግብርና ምርት በአለም ዙሪያ ለመላክ የትስስር ሰንሰለቶችን ይሰጣል። አርሶ አደሮች በምርት/በገበያዎች ላይ ምክር ያገኛሉ።
- አርሶ አደሮች ደላላዎችን በማስወገድ የቀጥታ ግብይት ውስጥ የሚገቡ ሲሆን ይህም ሙሉ ዋጋውን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል። ለስኬታቸው አርሶ አደሮች ጥበቃ ያገኛሉ።
- የአርሶ አደሩን መሬት መሸጥ፣ ማከራየት ወይም በዋስትና ማስያዝ የተከለከለ ነው፣ የአርሶ አደሩን መሬት በማናቸውም ማሻሻያ/ለውጥ እንዳይደረግበት ይጠበቃሉ። ቢዚህ ህግ ውስጥጥ የግጭት አፈታት ዘዴ አለ።

## ለአርሶ አደሩ ደህንነት ያለው ቁርጠኝነት

የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ እንደ መነቃቂያ ፕሮግራሙ ክፍል ተከታታይ ደረጃዎች ተጠቅሰዋል። እነዚህም የሚያካትቱት:-

- በኪሰን ክሬዲት ካርዶች በኩል የፈቃድ ክሬዲት
- በግብርና ትላላቅ ፕሮጀክቶች የፋይናንስ ፋሲሊቲ
- የአሳ አጥማጆችን ለማጠናከር Pradhan Mantri Matsya Sampada Yojana መጠቀም
- ለእግር እና አፍ በሽታዎች እና ለባክቴሪያ በሽታዎች ክትባት
- የአትክልት እና ፍራፍሬ ግብርና ማሳደግ
- የሙቀት ጥበቃውን ማሳደግ እና የአረንጓዴ ልማት ስራ ወዘተ

በዚህ በእንቅስቃሴ ገደብ ወቅት በጠቅላይ ሚኒስቴር ሂሳን በኩል 95.4 ሚሊዮን በላይ የግብርና ቤተሰቦች በ24/09/2012/ የተጠቀሙ ሲሆን እንዲሁም 195.2 ቢሊዮን ሩፒ ተከፋፍሏል።

# የፓን - ህንድ የትክክለኛ ጊዜ ሀይል ገበያ

Ministry Of External Affairs
Government Of India
ECONOMIC DIPLOMACY & STATES DIVISION

የህንድ መንግስት ለኤሌክትሪክ፣ ለህንዳዊያን የኤሌክትሪክ ገበያ በትክክለኛ ጊዜ ግብይት ባላቸው ጥቂት ሀገራት ሊግ ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ የፓን - ህንድ የትክክለኛ ጊዜ ግብይትን አቋቁሟል።

- የትክክለኛ ጊዜ ግብይቱ ገገሮዎች እና ሻጮች ወደ ትክክለኛ ጊዜ ስራ ለማቅረበ የሚያስፈልጋቸውን ሀይል እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።
- የትክክለኛ ጊዜ ግብይቱ የተመጣጣነ አቅርቦትን ለመስጠት ተለዋዋጭነት የሚያመጣ ሲሆን በስርዓቱ ውስጥ ተጨማሪ አቅምን መጠቀምን ያረጋግጣል።
- ስርዓቱ በህንድ ፍላጐት መሰረት ያሉትን ልዩነቶች የሚያስተናግድ ሲሆን እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ገበያውን የሚያቀናጅ እና የሀይል አቅርቦትን የሚያሻሽል ይሆናል

→ የትክክለኛ ጊዜው ግብይት በቀን ውስጥ ለ30 ደቂቃዎች ሲሆን ይህም በተመሳሳይ ዋጋ በሁለት ጐን ዝግ ጨረታ ላይ የተመሰረተ ነው።

→ "የበር መዘጋት" ጽንሰ ሃሳቡ በግብይቱ ሰዓት ውስጥ በፐሮግራም ውስጥ ፍላጐት ላላቸው ድርጅቶ የሚታወቅ ይሆናል .

→ ገቢዎች/ሻጮች የግዢ/የሽያጭ ጨረታዎችን ለእያንዳንዳቸው 15 ደቂቃ የመዝጋት አማራጭ አላቸው።

የተጠቀሰው የትክክለኛ ጊዜ ግብይት ለተጠቃሚዎች አማራጭን የሚሰጥ ሲሆን ይህም በተወዳዳሪ ዋጋዎች ላይ ሰፊ ገበያ ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

በሌላ በኩል ወጪ የሚያወጡ አካላት በማያጠያይቅ አቅማቸው በትክክለኛ ጊዜ ግብይት ውስጥ ከመሳተፍ የሚጠቀሙ ይሆናል።

የአሰራር ዘዴ ከተጠቃሚዎች ጋር የተጣራውን ገቢ እንዲጋሩ ለማድረግ የረዥም ጊዜ የግብይቱን ላላቸው ወጪ አውጪዎች ቀርቧል።

የትክክለኛ ጊዜ ግብይት ከተለያዩ የታዳሽ ሀይሉ ተፈጥሮ የተነሳ የሚኖሩትን ተግዳሮቶች የሚያስቀር ሲሆን በዚህም የተሻለ ጥምረትን ያረጋግጣል።

ይህም በበቂ የሀይል ግዢ/ፕሮግራም/መላ/የተመጣጠነ ቁጥጥር አገልግሎቶች የአስተዳደር መድረኩን ያሻሽላል።

# የተመላሽ ህንዳዊያንን ክህሎት መጠቀም

ወደ ህንድ የሚመለሱ የተማሩ ህንዳዊያንን ክህሎት በዚህ ባገጠመው ወረሽኝ ለመጠቀም አላማ መንግስት የተማሩ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ሰራተኞች መረጃን ለስራ ድጋፍ የሚለውን አሰራር ያዘጋጀ ሲሆን ይህም በቬንዴ ባህራት ተልዕኮ ስር የተመላሽ ዜጎችን ክህሎት ለመጠቀም የታለመ ነው፡፡

- የክህሎት ልማት እና የስራ ፈጠራ ሚኒስቴር፣ የሲቪላቬሽን ሚኒስቴር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተማሩ ዜጎችን የመረጃ ቋት ለመፍጠር በጋራ የሚሰሩበት ነው፡፡
- ባለው ክህሎት እና ልምድ መሰረት የመረጃ ቋቱ በህንድ ውስጥ ያሉትን የአሰሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት የሚጠቀም ይሆናል፡፡ የኤምኤስዲኢ ክፍል የብሔራዊ የክህሎት ልማድ ኮርፖሬሽን ፕሮጀክቱን የሚተገብር ይሆናል፡፡
- የተሰበሰበው መረጃ በሀገሪቱ ውስጥ ተስማሚ እድሎች እንዲኖሩ ለኩባንያዎች የሚጋራ ይሆናል፡፡ ተመላሽ ዜጎቹ በኦን ላየን የስዋዴስ ስኪል ካርድን መሙላት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ካርዱ ተመላሽ ህንዳዊያን ከባለድርሻ አካላት [illegible] አሰሪዎች ጋር በሚደረጉ ውይይቶች ተስማሚ ስራ ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻችላቸዋል፡፡
- ሁሉም ተመላሽ ዜጎች ስለተማሩ ተመላሽ ሰራተኞች መረጃ ቋት ለስራ ድጋፍ ማበረታቻው የሚያውቁ መሆናቸውን እና ጥቅሞቹን የሚያውቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በዲጂታል፣ በአካል ፊርማዎች እንዲሁም ከኤምባሲ ጋር በመገናኘት እና በመነጋገር ለማረጋገጥ ጥረት ይደረጋል፡፡

ከስደት ተመላሾቹ ሰለፕሮግራሙ የበለጠ ለማወቅ በኦንላየን www.nsdcindia.org/swades ቅጽ መሙላት ይችላሉ፡፡ የኦንላየን ስዋዴስ የክህሎት ቅጹ በግንቦት 30 እና ሰኔ 3 ባለው ጊዜ መካከል እስከ 7000 ተመዝጋቢዎች ደርሷል፡፡

በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ወደ ሀገሪቷ ለመመለስ እየጠየቁ በተለያዩ የህንድ ተልዕኮዎች ላይ ተመዝግቧል፡፡ እንዲሁም ከ57000 ህዝብ በላይ የሚሆኑት ወደ ሀገሪቱ ተመልሰዋል፡፡

# የቪዛ  እና የጉዞ ገደቦች  ማቅለያ

የህንድ መንግስት የቪዛ እና የጉዞ ገደቦች ማቅለያውም  ወደ ህንድ መምጣት ለሚፈልጉ እና  የውጭ ሀገር ዜግነት ላላቸው የተወሰኑ ቡድኖች ከግምት አስገብቷል፡፡  ከዚህ በታች ባሉ  ምድቦች  ውስጥ  ለሚገኙ  የውጭ  ሀገር  ዜጐች   ወደ  አንድ  ሀገር  እንዲመጡ ለመፍቀድ ተወስኗል፡፡

- በንግድ  ቪዛ ወደ ህንድ ሀገር የሚመጡ የውጭ ሀገር ነጋዴዎች (ለስፖርት ተግባራት ከሆኑት ከቢ-3  ቪዛ ውጭ)ፕሮግራም ባልተያዘለት የንግድ/የቻርተር በረራዎች

- የውጭ ሀገር የጤና ባለሙያዎች፣ የጤና ተመራማሪዎች፣ መሀንዲሶች እና ቴክኒሽያኖች የሆኑ እና በህንድ የጤና ዘርፍ ፋሲሊቲ ላይ በቴክኒክ ስራ  ይህም ለላብራቶሪዎች እና ፋብሪካዎች የሚመጡ፡፡ (ይህም በህንድ ውስጥ ከሚገኝ ከታወቀ እና  የተመዘገበ የጤና ተቋም፣ ከተመዘገበ የመድሀኒት  ማምረቻ ፋብሪካ ወይም ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ የግብዣ ደብዳቤ ማቅረብን ይጠይቃል)

- የውጭ ሀገር ምህንድስና ባለሙያ፣ ስራ አስኪያጅ፣ የዲዛይን ባለሙያ ወይም ሌሎች በህንድ ሀገር ውስጥ በሚገኙ የውጭ ሀገር የንግድ ስራዎችን ወደ ህንድ የሚጓዙ ባለሙያዎች  ይህ  የሚያካትተው  ሁሉንም  የማምረቻ  አካላት  የዲዛይን  አካላት፣ ሶፍትዌር፣ የአይቲ እቃዎች እና የፋይናንስ ዘርፍ ኩባንያዎችን (ባንክ እና  NBFC ድርጅቶችን) ነው፡፡

- የውጭ ሀገር የቴክኒክ ባለሙያዎች እና  መሀንዲሶች ሆነው በህንድ ሀገር ውስጥ ለሚገሁኑ የውጭ ሀገር ማሽነሪዎች ፣ የመሳሪያ ፋሲሊቲዎች፣ የዝርጋታ ስራ፣ የጥገና ስራ የማስተካከያ ስራን በመስራት በህንድ ውስጥ በተመዘገበ ኩባንያ ግብዣ ወደ ህንድ የሚጓዙ፡፡ (ይህም ለመሳሪያ መግጠም ወይም  በዋስትና ስር ወይም ከሽያጭ በኋላ ላለ አገልግሎት ወይም ለንግድ እቃዎች ጥገና ሊሆን ይችላል)

→ ለውጭ ሀገር ዜጐች የተቀመጡ ከላይ የተገለፁ  ምድቦች የሚያገለግል የንግድ ቪዛ ወይም የስራ ቪዛ ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን ይህም ከህንዳዊያን ተልዕኮዎች/የውጭ ሀገር ማስታወቂያዎች  ተግባራዊ የሚደረግ  ነው፡፡

→ የሚያገለግል የረጅም ጊዜ  ባለ ብዙ መግቢያ የንግድ ቪዛ ያላቸው የውጭ ሀገር ዜጐች /ለስፖርት ከሆነው የቢ-3 ቪዛ ውጭ/ በህንድ ተልዕኮዎች/በውጭ ሀገር ማስታወቂያዎች የተሰጣቸው ሁሉ ከህንድ ተልዕኮ/ከሚመለከተው አካል የንግድ ቪዛውን በድጋሚ የሚያገለግል ማስደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

→ የዚህ አይነት የውጭ ሀገር  ዜጐች አስቀድመው ባገኙት የኤሌክትሮኒክ ቪዛ ወደ ህንድ ሀገር መጓዝ አይፈቀድላቸውም፡፡

ለበለጠ  መረጃ: Link

# እናመሰግናለን

Ministry Of External Affairs
Government Of India

ECONOMIC
DIPLOMACY
& STATES
DIVISION